# በኢትዮጵያ ላይ ያንዣበበውን የውጭ ኃይሎች

# ሴራ እንዴት ለመቋቋም እንችላለን?

## ክፍል ሶስት

October 6, 2017 -



አክሎግ ቢራራ (ዶር)

–ካለፈው ታሪካችን በመማር–

አክሎግ ቢራራ (ዶር)

ያለፉት አምሳ ዓመታት የፖለቲካ ታሪካችን የሚያሳየን ግድፈት ወይንምድክመት (Failure) ካለፈው ተምረን የወደፊቱን ለማሻሻል
ሞክረንአናውቅም። የአቋም ግትርነት ከባህርያችን ጋር ተቆራኝቷል። በክፍል አንድና ሁለት የቀረቡትን ተግዳሮቶች ሰብሮ
ለመውጣትና  አቅጣጫዎችን ስኬታማለማድረግ የጋራ አገር አለን ማለትን፤
የጋራ ዓላማና እምነት አለን ማለትን፤የጋራ ብሄራዊ ዓላማ አለን ማለትን ይጠይቃል። ለጋራ የሃገር ደህንነትናቀጣይነት፤ ለጋራ ጥቅ
ምና ዘመናዊነት፤ ለጋራ ፍትሃዊና ዘላቂ እድገትተባብረን ለመስራት የምንወስንበት ወቅት አሁን ነው። ኢትዮጵያ ከፈረሰችናየእርስ በ
ርስ ግጭት ከተነሳ በኋላ አይደለም። ጊዜ የለንም። አምስትና አስርዓመታት እንጠብቅ፤ እንቆይ ካልን ኢትዮጵያን እናጣታለን!!
ኢትዮጵያን ለማዳን የምንችለው እኛው ብቻ ነን። ኢትዮጵያ ብትፈራስ አዲስ ህይወት እናገኛለን የሚሉ ወገኖች ተሳስተዋል። ገና ያ
ላዩት ነገር ይናፍቃል እንጅይህች አገር ከፈረሰች ከሶማልያና ከሶሪያ የየባሰ ሁኔታ ይከሰታል። በአዲስ አበባ ሆነ በሌላ ከተማ የምናየ
ው ሰማይ ጠቀስ ህንጻ፤ ተወዳዳሪ የሌለው ቪላ፤መሰረተ ልማት ወዘተርፈ ይወድማል።
ኢትዮጵያን እንድትፈርስ ያደረግናት ራሳችን ነን። ለከፋም ለደጉም ልምዱ አለን። የሚጠይቀው ከቡድን ወይንም ከፓርቲ ወይንም
ከጎሳ ወይንም ከኃይማኖትጥቅም በላይ ሃገርንና መላውን ሕዝቧን ማስቀደምን! ከመጠላለፍና እርስ በርስ ከመነታረክ በፊት መደማ
መጥንና መቻቻልን! አንዱ ከሌላው ለመማርፈቃደኛነትን! የእኔ አጀንዳ ይቅደም ከማለት በፊት እየተናበቡ በጋራ ብሄራዊ ዓላማ ላ
ይ የተመሰረተ የጋራ ራእይንና ተልእኮን ማመቻቸትን! ይሆናል። ይኼን ለማድረግ ያልቻልነው እኛው ነን። ፈረንጆች አስገድደውን
አይደለም።
ላለፈው ጥፋት ወይንም ድክመት ቂም በቀለኛነትን ማስተጋባት አያዋጣም። ያለፈው አልፏል። የአገራችን ሁኔታ የሚጠይቀው ጥፋ
ቶችን አምኖና ተቀብሎየመተማመንን ባህልን ማጠናከርን ነው። የድብቅ አጀንዳን ልማድ ከማድረግ ይልቅ ግልጽነትን፤ ሃላፊነትንና
ተጠያቂነትን የባህሎቻችን አካል ማድረግ ወዘተለዲሞክራሳዊ ስርዓት ግንባታ ወሳኝ ናቸው።
የአስተሳሰብ ለውጥ ወሳኝነት (The imperative of a paradigm shift)
ከተማሪው እንቅስቃሴ (1960s and early
1970s) ጀምሮ እስካሁን (2017) የተገነዘብኩት አንዱ ትምህርት እኛ "ምሁራንና ልሂቃን ነን" ብለን ራሳችንየምንሰይም ግለሰቦች

የሃሳብ መሪዎችና ቡድኖች ወደኋላ ዘወር ብለን በማሰብ “ምናልባት እኔኮ ተሳስቸ ይሆናል፤ የተናገርኩት ሌላውን ሰው አስቀይሞት ይሆናል፤ ለሃገራችን አደጋዎች ፈጣሪና አስተጋቢ ይሆናል” ለማለት የማንደፍር መሆናችንን ነው። የአስተሳሰብ ለውጥ ያስፈልጋል ስ ል “ምናልባት እኔ ተሳስቸይሆናል፤ እስኪ ከመናገር ማዳመጥንና ራሴን መመራመርን ላስቀድም” የሚለውንም እናስብበት ማለቴ ነ ው። ሌላውን ማማት፤ ሌላውን ማውገዝ መቆምአለበት!! መጀመሪያ የራሳችንን ስህተት እንቀበል!!

መኖር ብዙ ነገሮችን ያሳያል። የሌሎች አገሮችን ልምድ ማየት አስተሳሰብን ያሰፋል። እኛ ኢትዮጵያዊያን ከዚህ በፊት የተጓዝንባቸው ን የፖለቲካ መንገድግድፈቶች በጽሞና ብናጤናቸው ከራሳችን የፖለቲካ ታሪክ ብዙ ለመማር እንችል ነበር። ችግሩ ስህተቶችን መስ ራቱ አይደለም። ችግሩ ከስህተቶች ለመማርአለመቻላችን ነው። ከስህተት አለመማር በራሱ አስለች ነው። በተጨማሪ፤ የእኔ ትውል ለአሁኑና ለተከታታይ ትውልድ መንፈስን፤ ህይወትን፤ አገርንናህብረተሰብን የሚለውጡ ወይንም የሚያድሱ ሃሳቦችን ሊሸምት የሚ ያስችል ትምሕርት እንዲያገኝ አላስቻልነውም። የአሁኑና ተከታታይ ትውልድ ከብሄርተኛቻ፤ ከመናናቅ፤ ከምቀኝነት፤ ከቂም በቀልነ ት ምን ለማስተማር ይቻላል? አይቻልም።

ያለፈውን በግድፈት፤ በቂም በቀልነት፤ በጥላቻ ወዘተርፈ የተበከለ የፖለቲካ መንገድ ለአንድ ደቂቃ ዞር ብለን ብናስተውለውና ከአ ሁን በኋላ ከአብሮ መስራትውጭ ሌላ አማራጭ የለም! አገርንና ሕዝብን ከማስቀደም ሌላ አማራጭ የለም! ከመቻቻልና ለሌላው ግ ለሰብ፤ እንደ ኢትዮጵያዊነቱና እንደ ሰብእነቱ ከማሰብ፤“ነግ በእኔ” ከማለት (Empathy) የተሻለ ውጤት ሊያስገኝ የሚያስችል መን ገድ የለም! ብለን አብረንና ተባብረን ለመስራት ብንችል ለኢትዮጵያና ለመላውሕዝቧ ከፍተኛ አስተዋፆ ለማድረግ እንችላለን። ልዩነ ት ጤናማ ነው። ልዩነት እንዳለ ሆኖ፤ አንዱ ሌላውን ማዳመጥ፤ አንዱ ከሌላው ለመማር ፈቃደኛ ቢሆንለኢትዮጵያና ለመላው ሕዝ ቧ አዲስ ምእራፍ ይከፍታል። የማያዋጣው ጊዜ ያለፈበት መንገድ “የእኔ አስተሳሰብ፤ የእኔ ድርጅት” ብቻ (My Way or the Highway) የሚለው ጊዜ ያለፈበት ጎዳና ነው።

በተደጋጋሚ ከባለሞያዎች የምንሰማው እንዲህ የሚል ነው። “አንድ ግለሰብ ለመመራት ካልቻለና ፈቃደኛ ካልሆነ፤ ለመምራት አይ ችልም፤ የሞራል ብቃትየለውም። አንድ ግለሰብ ከሌላው ለመማር ካልቻለ ለማስተማር አይችልም፤ ራሱን ለመለወጥ አይችልም።” ራሳችን ለማሻሻል ስንል፤ ለትምህርት ያለንትጉህነትና ታታሪነት በጣም አስደናቂ ሆኖ ሳለ ከእርስ በርሳችን ለመማር፤ ለሃገርና ለሕዝ ብ ጥቅም ስንል ለመመራትና ሕብረተሰቡን ለማገልገል ያለን ፍላጎትበጣም ዝቅተኛ ነው። ይህ ከቀጠለ እውነተኛ ዲሞክራሲን ለመ መስረት አንችልም። ካልቻልን ኢትዮጵያ ትፈርሳለች፤ ከፈረሰች ሁሉም ኢትዮጵያዊያንይጎዳሉ። ዲሞክራሲ የቡድን፤ የማህበረሰብና የህብረተሰብ ስፖርት እንጅ የግለሰብ ስፖርት አይደለም። የአስተሳሰብ ለውጥ፤ መተባበርን፤ መተሳሰብን፤መደማመጥን፤ መደጋገፍን ወዘተርፈ ይጠይቃል።

በመተባበር፤ በመደጋገፍና በጋራ ጥቅም የተመሰረተ የፖለቲካና የእድገት ባህል ስር እንዲሰድ ከፈለግን መጀመሪያ የአስተሳሰብ ለው ጥ በማድረግ የኢትዮጵያንዘላቂነትና የስብጥር ሕዝቧን አንድነት የታሪክ ሂደት ተቀብለን፤ የኢትዮጵያንና የመላውን የኢትዮጵያን ሕ ዝብ ዘላቂ ጥቅም እናስቀድም ለሚል መርሆየማያወላውል ትኩረትና ቅድመት መስጠት ግዴታችን ነው።

ኢትዮጵያን እኛ ካላቀደምን ማን ሊያስቀድምልን ነው? የእያንዳንዱን ኢትዮጵያዊ መብት ካላስቀደምን ማን ሊያስቀድምልን ይችላል ? አንዱ ወገን በሌላው ላይየሚደረገውን ሃሜት፤ የጥላቻ መርዝና ሕዝብን መከፋፈል ስንሰማና ስናይ ለምን በድፍረት ይኼ ትክክል አይደለም ለማለት አንችልም? ብሄራዊ ጥቅምበመሸነጋገል ስኬታማ አይሆንም።

ብሄራዊና ሕዝባዊ ጥቅሞች ተቀዳሚ ይሁኑ ስል የሁሉም ብሄርና ኃይማኖት አባላት መብትና ጥቅም ይከበሩ ማለቴ ነው። የኢትዮ ጵያን ብሄራዊ ጥቅም፤የኢትዮጵያን ቀጣይነትና ሉዐላዊነት እናስቀድም የሚለው መርህ የሁሉም ብሄሮች ግዴታ ነው። ይኼን የጋራ ብሄራዊ ዓላማ የሚጻረሩትን ግለሰቦችና ቡድኖችደፍረን ለመተቸትና ለመናገር መቻል አለብን።

እኛ አገራችን ለቀን ወደ ሌላ አገር (አሜሪካ፤ ካናዳ፤ አውስትራሊያ፤ ጀርመኒ ወዘተ) ስንሰደድ የተሰደድንበትን አገር የሕዝብ ስርጭ ት፤ ባህል፤ ኃይማኖት፤ፖለቲካ ወዘተ ያለ ማመንታት እንቀበላለን። ሰዓትና አለቃ እናከብራለን። ለብዙዎቻችን የጋራ የሆነችውን እና ት አገር ታሪክና ሌላ ለመቀበል፤ አገር ወዳድመሪዎችን ለማፍራትና ለመንከባከብ በጣም ያስቸግረናል። በአገራችን ግፍና በደል ይፈ ጸማል ካልን በኋላ በካናዳ፤ በአሜሪካ፤ በአውሮፓና በሌሎች አገሮችአቤቱታ የምናቀርበው በተናጠል፤ በጎሳ፤ በኃይማኖትና በሌሎች መለያዎች ነው። አማራው ለአማራው!! ትግራዩ ለትግራዩ!! ኦሮሞው ለኦሮምው!! እ.ጂኩለራሱ ብሄር!! ሶማሌው ለራሱ ወዘተርፈ ይቁም የሚለው የማንነት መርህና አቋም ኢትዮጵያዊነትን አድክሞታል። ስለደከመም የምንጋራው እሴት የለምየሚለው ባህል ስር እ ንዲሰድ ተደርጓል።

የምንጋራት አገር አለችን ወይንስ የለችንም?

ላለፉት ሃያ ሰባት ዓመታት ኢትዮጵያን፤ የተፈጥሮ ኃብቷን፤ ባጀቷን በበላይነት ተቆጣጥረው በማንም አገር ታይቶ የማይታወቅ የግ ል፤ የቤተሰብና የፓርቲኃብት ያካበቱት ህወሓቶችና ተባባሪዎቻቸው ከዚህች ኃብትና ክብር ካስገኘችላቸው አገር ጋር ምን ተቃርኖ እንዳላቸው ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሚገልጹበትአዲስ የዘመን መለወጫ ዓመት በዓል እንዲከበር ህወሓት/ኢህአዴግ ሰብኳል፤ ሕዝቡ በዓሉን የሚያከብርበትን ሁኔታ ግን አላመቻቸም። የኢትዮጵያ ሕዝብ ገዢዎች ከሕዝቡ ጋር ተጣልተዋል የሚሉ ብዙ ናቸው። ከሕዝቡ ጋር ተቃርኖ ከሌላቸውና የኢትዮጵያ ሕዝብ ተቻችሎ እንዲኖርና ሁሉም ኢትዮጵያዊያን ከድህነት ነጻ ወጥተው ራሳቸውን እንዲችሉ ፍላጎት ካለ፤

አገሪቱን በክልል ለያይተው፤ አንቀጽ 39 መመሪያቸው አድርገው ወዘተ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይየጫኑትን ሕገ መንግሥት የሚቀይሩ በት፤ ቢያንስ የሚያሻሽሉበት ወቅት አሁን ነው። ጠባብ ብሄርተኝነት የማያዋጣና አገርንና ህብረተሰብን ከፋፋይ መሆኑንተቀብለው ኢትዮጵያዊነት የሚያኮራ የዜግነት መለያችን መሆኑን ይፋ የሚያደርጉበት ወቅት ዛሬ ነው።

እነዚህ አዲስ ባለ ኃብቶችና ባለሥልጣናት የኢትዮጵያና የመላው 105 ሚሊየን ሕዝቧ ባለ ውለታ ናቸው። ከድህነት ስቃይ ነጻ ያወጧቸው ኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ሕዝብ ናቸው።

ለሁለቱም ኃላፊነት አለባቸው። የመጀመሪያው ሃላፊነት የኢትዮጵያን ታሪክ ተቀብሎ ግዛታዊ አንድነቷን፤ ዳር ድንበሯን፤ቀጣይነቷን ፤ ብሄራዊ ጥቅሟን፤ ሉዐላዊነቷንና ክብሯን በማያሻማ ደረጃ ማክበርና ማስከበር ነው።

ጠባብ ብሄርተኝነት፤ ጎጠኝነት፤ አድሏዊነት ወዘተ ከቀጠለ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊያንን ወክሎ የሚናገር ማን አለ? የምንሰራውና የምንናገረው ሁሉኢትዮጱያን የሚያጠፋ ከሆነ የጋራ አገር አለን ለማለት የምንችልበት ሁኔታ የት ላይ ነው ያለው? ለዚህች ኢትዮጵ ያ ለምትባል አገር ማን አቤቱታ ያቅርብ? ወደተባበሩት መንግሥታት ብንሄድ ይስቁብናል!!

በዚህ ሁኔታ ወደፊት የሚከሰተውን ሳስብ እንቅልፍ አይዘኝም። የወደፊቱን (የዛሬ አምሳና መቶ ዓመታት) ስናጤን ዛሬ የምንኖርበት ዓለምና የወደፊቱ ዓለምበጣም የተለያዩ እንደሚሆኑ ማሰብ ግዴታችን ነው። ይህን የማይታወቅ ዓለም የልጅ ልጆቻችን እንዲዘጋጁ በት ከፈለግን ጠባብ ብሄርተኝነትን ማስወገድ፤አብሮና ተደጋግፎ መኖርን ማስቀደም ግዴታችን ነው። የሕዝብ ቁጥር እየጨመረ መ ሄዱ አይቀርም። የሕዝብ ቁጥር መጨመር በተናጠል ችግር አያመጣም።ችግር የሚፈጥረው መቻቻልና መግባባት አለመኖሩ ነው። ዛሬ የፖለቲካ በሽታችን ሁሉም "እኔ መሳፍንት ነኝ፤ ግዛቴና የተፈጥሮ ኃብቴ ይከበር ማለቱ ነው።" ከወገኑ ጋር ተቻችሎ ለመኖር የ ማይችል ሕዝብ የሚኖረው እጣ ሶማሊያን፤ ደቡብ ሱዳንን፤ አፍጋኒስታንን፤ ሶሪያን የሚመስል ነው። ኢትዮጵያዊያን በገፍአገራቸው ን የሚለቁበት ምክንያት ተስፋ ስለቆረጡ ነው። የወደፊቱን ዓለም "በአገራችን ሆነን ልንወጣው አንችልም" የሚል መልእክት እየላ ኩ ነው።

የወደፊቱን ዓለም የሚቆጣጠሩት ኃይሎች

ለዲሞክራሲ፤ ለፍትህ፤ ለሕግ የበላይነት፤ ለእውነተኛ እኩልነት፤ ችግሮችን በመወያየትና በመግባባት ለመፍታትለቆረጡ፤ ስግብግብነ ትን አስወግደው ያላቸውን የተፈጥሮና የገንዘብ አቅም ለጋርዮሽ ዓላማዎች ለማዋል የቆረጡ ሕብረተሰቦች ነው። ባለሞያዎች እንደ ሚሉት ወደፊት የሚከብሩትና አደጋዎችን የሚወጡት ዜጎች በማህበረሰባዊነት በጋራ ጥቅም የሚያምኑ ናቸው (Those with community and solidarity spirit). ከተሜነት እየተስፋፋ ሲሄድ በሕዝቦች መካከል ያለው ግንኙነት መቻቻልን፤ አብሮና ተካፍሎ መኖርን ይጠይቃል። በስግ ብግብነት የተበከለው የምእራብሊበራል ካፒታሊዝም ለዚህ ፍትሃዊ ለሆነ አዲስ ስርዓት የተዘጋጀ አለመሆኑን ሊቃውንት ሲተቹት ቆይተዋል። እነሱ ዓለምን የሚያሽረክሩት በየአገሩ እንሱንመሰል የጥቅም ሊሂቃንን (Social Elites) በመፍጠርና በመንከባከ መሆኑን ባለሞያዎች ይጠቅሳሉ። እነዚህ ለራሳቸው ጥቅም የፈጠሯቸው ማፊያ የሚመስሉቡድኖች የፖለቲካ ስልጣን እየያዙ ሽብርተኛ የሆነ የመንግሥት ስርዓት (Terrorist State and Government) መስርተው ሌላውን በሽብርተኛነትየሚከሱበትና የሚያሰቃዩበት ዋና ምክንያት የውጭ ደጋፊ ስላላቸው ነው። ሁለ ቱም ኃይሎች ለሃገር ወዳዶችና ለማህበረሰባዊ ዲሞክራሲ (Social and Participatory Democracy ጠላት ናቸው። (Robert Gaylon Ross, The Men Who Really Run the World, H. Paul Jeffers, History's Greatest Conspiracies. በጀፈርስ (Jeffers) ጥናት መሰረት እንደምናየው አሜሪካኖች ታዳጊ አገሮችን ለራሳቸው ጥቅም አመች በሆነ ስልት ለመቆጣጠር የ ቻሉት በሚፈልጓቸውአገሮች የጥቅም ተባባሪዎችን በመፍጠር ነው። ይህ የሚደረገው በዘፈቀደ አይደለም። በብዙ ጥናት፤ ምርምርና ውይይት ነው። "International elites of politics, industry, commerce, diplomacy, leaders of the

communications and news media, intellectuals; and the military" and global bodies such as the IMF, the World Bank, WTO, the World Court and numerous others are part of the humongous non-elected body of people and institutions that run the world" convene in secret and in public and manage our complex world in accordance with their own needs.

በተለይ፤ የአሜሪካኖች የበላይነት በዶሚኒካን ሪፐብሊክ፤ በኢራክ፤ በአፍጋኒስታን፤ በሻሁ መንግሥት በኢራን፤ በግብጽ፤ በደቡብ ኮሪያናበሌሎች አገሮች የሚካሄደው አገር ወዳድ መንግሥታትን በመገልበጥና ለአሜሪካኖች አመች በሆኑ ቡድኖች በመተካት ነው። የሃሳብ ተቋሞችና "የበጎአድራጊዎች (Good Samaritans) ዋና ስራም ይኼው ነው። "The annual and exclusive retreat of America's elites, the rich and powerful, including U.S. Presidents, cabinet officials, directors and officers of corporations, bankers, financiers, military contractors, leaders of the oil industry and nuclear power companies, and journalists" is not to make the world a better place for the billions of people who inhabit this planet. It is to preserve power, privilege and influence.

በዳቮስ (Davos) ሆነ በአሜሪካ በሚደረገው የግል ስብሰባ ኃይልና ኃብት ያላቸው ግለሰቦች ሲሰበሰቡና ሲመካከሩ የበለጠ ኃይለኛ ፤ የበለጠ ኃብታምይሆናሉ። በተባበሩት መንግሥታት ተቋማትም ያለው ሁኔታ የተለየ አይደለም። እኛ እርስ በርሳችን እየተባላን እነዚህ ኃይሎች ጥቅማቸውን ይስከብራሉ።

ኢትዮጵያ ብዙ ፈተናዎችን ያለፈችና አሁንም በብዙ ፈተናዎች የተበከለች አገር ናት። ይኼን ሃተታ እንድጽፍ የተገደድኩበት አበይት ምክንያት ይህች ረዥምታሪክ ያላት፤ ታላቅና ለሁሉም ዜጎቿ የሚበቃ የተፈጥሮ ኃብት ያላት አገር በራሷ ልጆች ስትጠቃ ማየቴ ነው። ፊት ለፊት የሚታገሉላትና ደፍረው ለታላቅነቷ፤ለቀጣይነቷና ለሉዐላዊነቷ የቆሙላት እየቀነሱ፤ እንደ ህወሓት ፊት ለፊት አትራፊና ዘራፊ ሆነው ኃብት እያካበቱና ከጀርባ ሆነው ታላቋ ኢትዮጵያ "ትንሽ" አገርእንድትሆን ቀን ከሌት የሚሰሩት እየጨመሩ ሲሄዱ የቀድሞ አባቶቻችንና እናቶቻችን ምን "ሃጢያት" ሰርተው ይሆን? የሚል ጥያቄ አነሳለሁ። ለዚህ መልስለማግኘት ቀላል ስለሆነ የታሪክ መጻህፍቶችን አነባለሁ። ታሪካችን የሚያኮራ መሆኑን እንደ ገና አረጋግጬ ችግሩን የፈጠርነው "እኛው ነን" ወደሚለውየተለመደ ድምዳሜ አመራለሁ። ከዚያም መፍትሄውን ከእኛ ሌላ ማንም ሊሰጠን አይችልም እላለሁ።

ያለፈውና የአሁኑ የኢትዮጵያ ታሪክ የሚነግረን ታሪክ የውጭ ኃያላን መንግሥታት፤ ድርጅቶችና ግለሰቦች አገር ቤት ካሉት ጋር በመመሳጠር ኢትዮጵያ ነጻ፤የተከበረች፤ የተባበረችና ኃብታም አገር እንዳትሆን ብዙ ሴራዎችን አካሂደውባታል፤ አሁንም እያካሄዱባት ነው። ይህን የሚያደርጉት ተጠቃሚዎችንበመፍጠር፤ በየድርጅቱ በማስገባት፤ መሸሽጊዎች በማመቻቸት ወዘተ ነው። ይህን ግዙፍ ችግር ልንፈታው የምንችለው በአሁኑ የብሄር/ቋንቋ ፌደራሊዝምስርዓት ሊሆን አይችልም። በመከፋፈልና በመበታተን ሊሆን አይችልም። ሕዝቡ የፖለቲካ ስልጣኑ ባለቤት እንዲሆን በማመቻቸት፤ የሃገራችን የተፈጥሮኃብት ለሁሉም ኢትዮጵያዊያን ጥቅም እንዲውል ያልተቆጠበ ጥረት በማድረግ ብቻ ነው። ይህን ለማድረግ እውነተኛ ዲሞክራሲ አስፈላጊ ሆኗል።

ህወሓት/ኢህአዴግ ሰላምን፤ መቻቻልን፤ እርጋታን አይፈልግም። ያስጠቃኛል የሚል ግምትና እምነት አለው። የኢትዮጵያን ቀጣይነትና ሉዐላዊነት ያለማወላወል አይቀበልም። በኦሮሞና በሶማሌ ብሄር ኢትዮጵያውያን መካከል የእርስ በርስ ግጭት ኢንዲካሄድ የፈቀደውና ያመቻቸው እርጋትና ስለማፈልግ ነው። እነዚህን ጠቃሚ መርሆዎች ማስከበር የምንችለው እኛው ነን። ይህን ለማድረግ የምንችለው በመተባበርና አብሮ በመስራት ነው።

በተጨማሪ፤ የውጭ ጠላቶችን ከበባንም ለመቋቋምና ለማጋለጥ የምንችለው እኛው ነን። ይኼን ከበባ ለመቋቋም ከቆረጥን ከሌሎች የአፍሪካ ቀንድ ጎረቤት አገሮች ተወላጆች ጋር መቀራረብና አብረን መስራት አለብን። ከበባው የሚያስጠቃው የኢትዮጵያን ሕዝብ ብቻ አይደለም። መላውን የአፍሪካን ቀንድ ተወላጆች ጭምር ነው።

ኢትዮጵያ ተብላ የምትታወቀው ሃገራችን ከተመሰረተችበት ከአራት ሽህ ዓመታት በፊት ጀምሮ የኢትዮጵያ የውጭ ጠላቶች ኢትዮጵያን ለማፈራረስ፤ ዘላቂጥቅሞቿን ለመንጠቅ፤ ዳር ድንበሯ እንዳይከበር ለማድረግ፤ ብሄራዊ የሆነ ጠንካራና ዘመናዊ ኢኮኖሚ እንዳ ይመሰረት ለማድረግ ወዘተ ያልሞከሩት ተንኮልየለም። መልኩንና ዘዴውን ይቀይራል እንጅ፤ ሴራው ወደፊትም ይቀጥላል።

የውጭ ኃይሎች ኢትዮጵያን ለምን ከበቧት?

ጥያቄውን ሙሉ በሙሉ ለመመለስ አልሞክርም። ቦታው አይደለም። ሆኖም፤ አራት ቁልፍና ለአገር ቀጣይነት እና እድገት ወሳኝ፤ ለውጭ ግኑኝነትና ለግጭትመንስኤ የሆኑ የተፈጥሮ ጥሪቶችን (Geographic as well as Natural Resources

Assets) ለመጥቀስ እገደዳለሁ።

1. የኢትዮጵያ ስትራተጂክ የጅኦግራፊ አቀማመጥ፤
2. የኢትዮጵያ ሰፊ ለም መሬት፤ ወንዞች፤ ዝናብና ሌላ የተፈጥሮ ኃብት፤
3. የኢትዮጵያ ረጂም ታሪክና የሕዝቧ አገር ወዳድነት፤
4. ኢትዮጵያ በቀይ ባህር ያላት ታሪካዊና ተፈጥሯዊ ሙብት።

ባለሞያዎች ስለ አፍሪካ ሲጽፉ “የተፈጥሮ ኃብት እርግማን ነው” ይላሉ። በአብዛኛው “እርግማን” ነው። አባይን እርግማን ነው ለማለት አልችልም። የዓባይናሌሎች ወንዞች ለኢትዮጲያ እድገት ወሳኝ ናቸው። ሆኖም፤ እንደ ዓባይ ያሉት ታላላቅ ወንዞች ወደ ኃይል ማመንጫና ወደ መስኖ ግድብ ሲቀየሩ እንደ ግብጽያሉትን አገሮች ስለሚያስደነግጡ አደጋዎችን መጋበዛቸው የማይቀር ነው። ለዚህ ነው በጽሁፎቼ የኢትዮጵያ ገዥ ፓርቲ ኢትዮጵያዊያንን መከፋፈል የለበትምያልኩት። አሁንም ለመደጋገም፤ ለኢትዮጵያ ዋና ዋስትናዋ የሕዝቧ አንድነትና እድገት ነው። የተፈጥሮ ኃብት ዋና ጥቅሙ የሕዝቡን ህይወት ማሻሻሉ ነው።የጥቂቶችን ኪስ መሙላቱ አይደለም!!

በተፈጥሮ ኃብት የታወቀችው ኮንጎ ኪንሻሳ ወይንም ዛየር ነጻ ከመውጣቷ በፊትና ከወጣች በኋላ ሰላምና እርጋታ አግኝታ አታውቅም። የውጭ መንግሥታት፤ድርጅቶችና ግለሰቦች የተፈጥሮ ኃብቷን እየነጠቋት ነው። ይህች ኃብታም ለመሆን የምትችል አገር ወዳድና ዲሞክራሳዊ መንግሥት እንዳይመሰረት ከፍተኛሴራ ሲካሄድባት የቆየች አገር ናት። እንደ አንጎላ፤ ናይጀሪያ፤ ካሜሩን፤ ጋቦን፤ ጊኒ የመሳሰሉት ነዳጅ አምራች አገሮች በመጥፎ አስተዳደር፤ በአድልዎና በሙስናስለተበከሉ ተራው ሕዝብ ከተፈጥሮ ኃብቱ ጥቅም አግኝቷል ለማለት አይቻልም። ይህ በአፍሪካ አገሮች የሚታየውን በመጥፎ አገዛዝ የተበከለውን አንዱን ጎንያሳያል፤ ሌላም ጎን አለ!! ይኼ መልካም አስተዳደር ወይንም ዲሞክራሳዊ ጎን ነው።

እንደ ቦትስዋና ያሉ የመንግሥት ስርዓታቸውን ያስተካከሉ ዲሞክራሳዊ አገሮች የተፈጥሮ ኃብታቸውን ለማህበረሰባዊ አገልግሎት አውለው አስደናቂ የእድገትውጤቶች አሳይተዋል። ከፍተኛ ገቢ አላቸው ከሚባሉት አገሮች ማካከል ቦትስዋና፤ ሞሪሺየስ፤ ሴሸልስ፤ ደቡብ አፍሪካ ይገኙበታል። ላወቀበት የተፈጥሮኃብት ለዘላቂና ለፍትሃዊ እድገት ወሳኝ ነው።

ሆኖም፤ የአገዛዝ ስርዓቱ አሳታፊ፤ ፍትሃዊ፤ ግልጽነትና ሃላፊነት ያለው፤ ዲሞክራሳዊ ካልሆነ የተፈጥሮ ኃብት ፋይዳ ቢስ ነው። ኢትዮጵያ ብዙ ጥሪቶች ያሏትአገር ሆና እስካሁን የምግብ ጥገኛ የሆነችበት ዋና ምክንያት ፍትሃዊ የሆነ አገዛዝ ስለሌላት ነው።

በእኔ እምነት፤ የኢትዮጵያ ማህበረሰባዊ
ጥሪቶች ከነዳጅ፤ ከእንቁና ከሌላ የበለጠ ጥቅም እንዳላቸው አምናለሁ። እኔን ያሳሰበኝ፤ ይህን እምቅ ኃብት በማባከንላይ ያለው
ገዢው ፓርቲ ብቻ ሳይሆን እኛው ራሳችን ተጨማሪና አጋር
መሆናችን ነው። ገዢው ፓርቲ ያባክናል፤ እኛም ጥሩ አማራጭ ለመስጠትአልቻልንም። የኢትዮጵያን እምቅ ኃብትና አቅም የሚያውቁ የውጭና የአገር ውስጥ ተቀናቃኞች ኢትዮጵያ ተፈጥሮ ያበረከቷትን፤ ተከታታይ ትውልድመስዋእት ሆኖ ያቆየውን ኃብቷን ተጠቅማ ራሱን የቻለና ጠንካራ ማህበረሰብ እንዳትመሰርት ማነቆ ሆነው ቆይተዋል። እኛም ደፍረን ይህን ተንኮል አቁሙለማለት አልቻልንም። ምክንያቱም ተከፋፍለናል። እርስ በርሳችን እንነታረካለን። መከፋፈላችን ለውጭ ጠላቶች አመች ሁኔታን ፈጥሯል።

ካለፈው ጥፋት እንማር

በእኔ ግምት በኢትዮጵያ ላይ ያልተጸነሰ፤ ያልታቀደ፤ ያልተቀናጀና ያልተካሄደ ሴራ (Conspiracy) የለም። በተለያዩ ወቅቶች የተለያዩ የውጭ ኃሎችኢትዮጵያን ግዛታቸው ለማድረግ ሞክረው በጀግናው የኢትዮጵያ ሕዝብ ቆራጥነትና ህብረት ሴራቸው ሳይሳካ ቀርቷል። ምንም እንኳን ብዙ የሰው፤ የከብትናሌላ የተፈጥሮ ኃብት፤ የማይተኩ የአገር ቅርሶችና ሌላ ኃብትና ጥሪት ቢያወድሙም ኢትዮጵያን ኃይል ተጠቅመው ሊገዟት አልቻሉም። ይኼ የኢትዮጵያሕዝብ ጥንካሬ ምልክት ወይንም እሴት ነው። በትሪሊየን ዶላር ሊገዛ አይችልም።

ኢትዮጵያን ለማሸነፍ መጥቶ በህይወቱ ወደ አገሩ የተመለስ የግብጽ ተወላጅ ወይንም ፈረንጅ ለማግኘት ያስቸግራል። ግብጾች ይህን ሃቅ ያውቃሉ። ለዚህ ነውየአገር ውስጥ ደጋፊዎች እየፈለጉ እኛን የሚያጠቁን። በኢትዮጵያና በግብጽ ሕዝብ መካከል ጥንታዊ የሆነ ግኑነት መኖሩን ታሪክ ይመሰክራል። የግብጽ ስልጣኔየኢትዮጵያ በረከት መሆኑን አንርሳ!! አባይ ይባላል።

አዶልፍ ፓርለሳክ (ተርጓሚ ጀብሬ መኮንን)

“የሃበሻ ጀብዱ” እና ኮ/ል አሌሃንድሮ ዴል ባዮ (ተርጓሚ ዶ/ር ተስፋየ መኮንን ባይለየኝ)

“ቀይ አንበሳ” በተባሉትመጻህፍቶቻቸው እንዳስተማሩን፤ ኢትዮጵያ “ለእኔ ትገባኛለች” ብሎ ከሌሎች የአውሮፓ ቅኝ ገዢዎች ጋር

ተመሳጥሮ ኢትዮጵያን የወረረው የጣሊያንመንግሥት በጀግናው በኢትዮጵያ ሕዝብ ብርታት፤ ህብረትና ቆራጥነት፤ በመጀመሪያ በአ ጼ ምኒልክ አስደናቂና ብልሃት የተሞላበት አመራር በአድዋ ተሸንፎያልሞተውን ወራሪ የጣሊያን መንግሥት መርከቦች ተጠቅሞ ወ ደ አገሩ መልሷቸዋል። በሁለተኛው ዙር የጣሊያን ወረራ የኢትዮጵያ አርበኞች ተስፋሳይቆርጡ አገራቸውን ከፋሽስቶች መንጋጋ ነጻ ለማውጣት ችለዋል።

ማሰብ ያለብን እንደዚህ የሚያኮራ ታሪክ ያላት ኢትዮጵያ ድህነትን፤ ጥገኝነትን፤ ኋላ ቀርነትንም ለማሸነፍ እነደምትችል ነው። ኦሮ ሞው፤ አማራው፤ ትግራዩ፤አፏኩ፤ አፋሩ፤ ጉራጌውና ሌላው ኢትዮጵያዊ በዚህ ሊኮራ ይገባዋል!!

ህወሓቶች/ኢህአዴጎች ሲመጻደቁብን እድገትን፤ ተሃድሶን የጀመርን እኛ ነን ይሉናል። የሰው ልጆችንም "እኛ ፈጠርን" ቢሉ አያስገር ምም። ሻቢያ፤ አነግናህወሓት ኢትዮጵያ "የመቶ ዓመታት ታሪክ ነው ያላት" ሲሉ ነው ይህችን አገር ሊያፈርሷት ተነስተዋል ብለን መነሳት የነበረብን። ስብሃት ነጋ የትምክህተኞችምሽግና መሰረት የሆኑትን "የኢትዮጵያ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንና የአማራውን ብሄረ ሰብ" በማያንሰራሩበት ደረጃ "አድቅቀናቸዋል" ሲል ነው አዲስ የኃይማኖትታሪክ፤ አዲስ የኢትዮጵያ ታሪክ እንዲጻፍ ወስነዋል ብለ ን መረባረብና መታገል የነበረብን። ዛሬ አንዳንድ "የኦሮሞ ጠባብ ብሄርተኞችና የውጭ ደጋፊዎቻቸው" ኢትዮጵያ የሚለውን ስም ፈጽሞ ለማጥፋት የተቀነባበረ ዘመቻ ይዘዋል። ኢትዮጵያን ሰርዞ "ኩሽ" ብሎ ለመሰየም፤ ለኢትዮጵያ ደጋግሞ እውቅና የሚሰጠው መጽሃፍ ቅድሱ ተቀይሮ ኩሽና ሱዳን የሚሉት እንዲተኩበት እየተደረገ ነው። እነዚህ አብዛኛውን የኦሮሞ ሕዝብ አይወክሉም።

የዛሬ ሰላሳ ዓመት ተመሳሳይ ጥረት ተደርጎ የኢትዮጵያ የክርስትና፤ የእስልምናና የሌሎች መንፈሳዊ መሪዎችና አባቶች ተሰብብሰውና ተመካክረው ይህ ሴራለአገሪቱና ለሁሉም ኃይማኖቶች አደገኛ ስለሆነ ለዓለም አብያተ ክርስቲያን ተቋሞችና ለሁሉም ለሚመለከታ ቸው ተቋሞች የሚረዳ ጠንካራ አቋም የያዘ አቋምተወስዶ፤ የአቤቱታ ደብዳቤ ተጽፎ ይህ ወንጀል ትክክል አለመሆኑ ተረጋግጦ የተ ጻፉት መጻህፍቶች ሁሉ እንዳይበተኑ ተደርጎ ነበር። ከሰላሳ ዓመታት በኋላአዲስ ምርምር፤ አዲስ የመጽሃፍ ቅዱስ ትርጉም፤ አዲስ የ አገር ስያሜ እንዲካሄድ ለምን እንደ ተደረገ ሰፊ ጥናትና ውይይት በአስቸኳይ መካሄድ አለበት።

ይህ አዲስ ክስተት የገዢው ፓርቲ እጅ አለበት ወይንስ የለበትም የሚለውን ለጊዜው አልፈዋለሁ። በአጭሩ ለማለት የምገደደው ው ሸት ተደጋጋሚ ሲሆንእውነት ይሆናል። እድገትን እኛ ጀመርነው የሚለው ውሸት ነው። የኢትዮጵያ ታሪክ የመቶ ዓመት ታሪክ ነው የሚለው ውሸት ነው።

ዘመናዊነት በህወሓት/ኢህአዴግ አልተጀመረም

አጼ ምኒልክ የአድዋ ድል መሪ ብቻ አልነበሩም። ከአጼ ቴዎድሮስ በኋላ ኢትዮጵያን በሁሉም የኢኮኖሚ ክፍሎች ዘመናዊ ለማድረ ግ እቅድ አውጥተውየእድገት መሰረት የጣሉት እሳቸው ናቸው። በጦርነቱ በኩል የአጼ ምኒልክ ድል ኢትዮጵያዊያንን ያስተማረን አ ንድ የጥቁር መንግሥት የነጭን መንግሥትበጦርነት ሲያሸንፍ ኢትዮጵያ የመጀመሪያዋ መሆኗን ነው። ግን ያደረጉት ይኼ ብቻ አይ ደለም። የትምህርት፤ የኢንቬስትመንት፤ የሃዲድ፤ የዘመናዊ መንገድ፤የመገናኛ ብዙሃን፤ የውጭ ግንኙነት፤ የማእደን ልማት፤ የንግድ፤ የባንክና የኢንዱስትሪ መስፋፋት ስራ የተጀመረው በእሳቸው ዘመነ መንግሥት ነው። እኛኢትዮጵያዊያን መሪዎች የሉንም ስንል ያሳ ፍራል፤ መሪዎች ነበሩን።

አጼ ቴዎድሮስ፤ አጼ ዮሃንስ፤ አጼ ምኒልክ፤ አጼ ኃይለ ሥላሴ የኢትዮጵያ ታላላቅ መሪዎች ናቸው። እነዚህ አገር ወዳድ መሪዎች እ ንደ ጣሊያኖች ያሉ የውጭጠላቶች ኢትዮጵያን የፈለጉበትና የወረሩበት ዋና ምክንያት የራሳቸውን የስራ እድል፤ የኢኮኖሚ፤ የንግድ ፤ የገበያና የተፈጥሮ ኃብት ፍላጎት ለማሟላት ነውእንጅ ለእኛ ስልጣኔን ለማምጣት አለመሆኑን ሙሉ በሙሉ ያውቁ ነበር። ለምሳሌ ኢትዮጵያ የክርስትና ኃይማኖትን የተቀበለችና የነቢዩ ሞሃመድን እምነት ተከታዮች ተቀብላ ያስተናገደች አገር መሆኗ እየታ ወቀ፤ ፈረንጆች ክርስትናእንዲስፋፋ ለማድረግ የሞከሩበት ምክንያት ለምንድን ነው? እነዚህ መንግሥታት ኢትዮጵያ ዘመናዊ መሆን እንዳለባትና ዘመናዊ ለመሆን እንደምትችልያውቁና የምኑ ነበር። ስለሆነም፤ ኢትዮጵያዊያን ከተስማማን አገራችንን ለማልማትና ዘ መናዊ ለማድረግ እንችላለን። ግን መርሳት የሌለብን አስኳል ጉዳይ አለ።ይኼውም፤ የአውሮፓ መንግሥታት የጣልያንን ፋሽዝም ለ መቃወም ያልደፈሩበት ዋና ምክንያት አድዋን በማስታወስ ኢትዮጵያ ጣልያንን ለማሸነፍ ከቻለችእኛ ከደረስንበት ደረጃ የመድረስ እ ድል ሊኖራት ይችላል በሚል ግምት ይሆናል የሚል እምነት አለኝ።

ለእኔ የአድዋ ድል የሚያመልከተው እንደ አጼ ምኒልክ አስተዋይ፤ አገር ወዳድ፤ ሁሉን አስተናጋጅና ዘመናዊ የሆነ አመራር ያላት ኢ ትዮጵያን ብንመሰርት፤ኢትዮጵያ ልክ እንደ ጃፓን፤ በአጭር ጊዜ ዘመናዊ ለመሆን ትችላለች። ለዚህ ነው፤ የአድዋ ድል ለጣሊያኖች ብቻ ሳይሆን ለሌሎች ነጮች፤ በተለይ ለአውሮፓቅኝ ገዢዎች የማይረሳ "ጥቁር ቀለም" እንደ ነበር ይታወቃል የምለው። በእኔ ግም ገማ የጣሊያንና የአውሮፓ ቅኝ ገዢዎች ሲገመግሙ "ኢትዮጵያ አሁን ባላትየኢኮኖሚና የመሳሪያ አቅም ጣሊያንን ለማሸነፍ ከቻለች

ወደፊት ምን ልትሆን ትችላለች? ይህች አገር ዘመናዊ ከሆነች ከእኛ ጋር ልትወዳደር ትችል ይሆን? በአፍሪካ ቀንድ፤ በቀይ ባህር፤ በሌላው አፍሪካ ተወዳዳሪ ትሆናለች!! ኢትዮጵያ ጃፓንን ለመሆን ምን ይጎድላታል? የሚሉ ጥያቄዎችን በምስጢርእንዳስተናገዱ እገምታለሁ።
ሙሶሎኒ ኢትዮጵያን ሁለተኛ ጊዜ ሲወር በአውሮፓ ተመጣጣኝ የሌለው የአየር ኃይልና ሌላ ዘመናዊ የጦር ኃይል አዘጋጅቶ ነው። ይህን ያደረገበት ዋናምክንያት ኢትዮጵያን ለመቅበርና የተፈጥሮ ኃብቷን በበላይነት ለመቆጣጠር ነው። ትኩረት ካደረገባቸው ጉዳዮች አንዱ አገሪቱን በጎሳ ከፋፍሎ ኢትዮጵያዊነትእንዲጠፋ ማድረጉ ነበር። ገዢው ፓርቲ ከቅኝ ገዢዎች የቀዳውን “የከፋፍለህ ግዛው” ስርዓት በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ጭኗል የሚባለው ለዚህ ነው።
መልኩ ይቀያይር እንጅ አሁንም ያለው የከበባ ሁኔታ ከዱሮው አይለይም። የአረብ መንግሥታት፤ በተለይ ግብጽና ሱዳን ኢትዮጵያ የአባይን ወንዝ ገድባ ለራሷዘመናዊነት፤ የኢንዱስትሪ ልማት፤ ብሄራዊ የምግብ ዋስትና ስኬታማነትና ለመላው ሕዝቧ የኢኮኖሚ ጥቅም ለማዋል እንዳትችል ብዙ መሳናክሎችንፈጥረውላታል፤ እየፈጠሩላት ነው፤ ወደፊትም ይፈጥሩላታል።
አንድ አገር በእርዳታ ብቻ ዘመናዊ አይሆንም። አሜሪካኖች የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ መሰረት ዘመናዊ እንዲሆን ምን የረባ ነገር ሰርተዋል? ከኢትዮጵያ በገፍየሚሰረቀውና የሚሸሸው ኃብት ወደ ራሳቸው ባንኮችና ሌሎች የኢንቬስትመንት እድል ያላቸው ቦታዎች እንዳይሄዱ ምን ጫና አድርገዋል? ለዚህ ሁሉተግዳሮት (Challenge) ብሄራዊ ድክመትና ውርደት መጋቢ የሆነው የራሳችን መከፋፈልና ገዢው ፓርቲ ነው።
የኢትዮጵያ ረዢም የሥልጣኔ፤ የንግድ፤ የሕዝብ እንቅስቃሴና ስርጭት፤ የኃይማኖት፤ የባህልና ሌላ ታሪክ ከባህር፤ በተለይ ከቀይ ባህር ወሰኗና ወደቧ ታሪኳጋር ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት አለው። የኢትዮጵያ ግዛቶች ከባህር ማዶ እስከ የመንና እስከ ሳውዲ አረቢያ ይጠጉ እንደነበር የታሪክ ባለሞያዎች ያስተምሩናል።ይህ የባህር በር ባለቤትነትና ይገባኛልነት በዓረብ መንግሥታት በኩል ተቀባይነት አግኝቶ አያውቅም። ለምሳሌ፤ በአምሳዎቹ፤ በስድሳዎቹና በሰባዎቹ ዓመታትግብጽ ኢትዮጵያ የወንዞቿንና የባህር ድንበሮቿን ባለቤትነት አረጋግጣ የዘመናዊነት እንቅስቃሴዋን ስታካሂድ ከሌሎች የዓረብ አገሮችና በአገር ውስጥለመገንጠል መንቀሳቀስ ከጀመሩ ግንባሮች ጋር አብረውና ተባብረው የኢትዮጵያን የባህር በር እንዲዘጋ ለማድረግ ችለዋል። በዚህ ሴራ ተባባሪ የሆኑት ግንባርቀደም መንግሥታት ግብጽ፤ ኢራክ፤ ሶሪያ፤ የፍልስጤም ሕዝቦች ግንባር፤ ሳውዲ አረቢያ፤ ጆርዳን፤ ሌባኖንና ሊቢያ ናቸው። እነዚህ መንግሥታት ዓላማቸውንስኬታማ ለማድረግ የቻሉበት ዋና ዘዴ የኤርትራን ነጻ አውጭ ግንባር፤ በኋላ የኤርትራ ሕዝቦች ነጻ አውጭ ግንባር (ሻቢያ) ተብሎ ለሚጠራው የተገንጣይቡድን ያልተቆጠበ የዲፕሎማሲ፤ የመረጃ፤ የመሳሪያ፤ የገንዘብ፤ የመሸሸጊያና ሌላ ድጋፍ በመስጠት ነው።
October 5,2017